በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

የመጀመሪያ ሳምንት

ምዕራፍ -3 የክፍልፋዮች ፣ አስርዩሽና አራቱ መሠረታዊ ስልቶች

ማስታወሻ፡- የሁለት ክፍልፋዮች ብዜት የምንለው የተሰጡትን ክፍልፋዮች ስዕሉን ከላዕሉ ጋር በማባዛትና ታህቱን ከታህቱ ጋር በማባዛት የሚገኝ ውጤት ነው።ለ እና ሠ≠ 0 ቢሆን $\frac{ሀ}{ለ} \times \frac{መ}{ሠ} = \frac{ሀ \times መ}{ለ \times ሠ} = \frac{ሀመ}{ለሠ}$ እውነት ነው።

ለምሳሌ፡- $\frac{1}{3} \times \frac{4}{5} = \frac{1 \times 4}{3 \times 5} = \frac{4}{15}$

1. $\frac{7}{4} \times \frac{4}{5} =$ .....

ማስታወሻ፡- ድብልቅ ቁጥሮችን ለማባዛት እያንዳንዱን ድብልቅ ቁጥር ወደ ህገወጥ ክፍልፋይ በመቀየር ስዕሉን ከስዕሉ፣ ታህቱን ከታህቱ ጋር በማባዛት የሚገኘውን ውጤት ማስቀመጥ ነው።

2. $2\frac{1}{3} \times 1\frac{2}{5} =$ .....
3. $3\frac{1}{5} \times 4\frac{1}{3} =$ .....

ህገኛ ክፍልፋዮችን ማካፈል

- **ደረጃ 1.** አካፋዮችን ገልብጡ (ታህቱን ላዕል እንዲሁም ላዕሉን ታህት አድርጉ) የተገለበጠው አካፋይ ተገላቢጦሽ ይባላል።
- **ደረጃ 2.** ክፍልፋዮችን አባዙ።
- **ደረጃ 3፡-** መልሱን በዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል አካፍሉ።ምሳሌ $\frac{2}{3} \div \frac{4}{5} = \frac{2}{3} \times \frac{5}{4} = \frac{2 \times 5}{3 \times 4} = \frac{10}{12} = \frac{5}{6}$

ድብልቅ ቁጥሮችን ማካፈል

ደረጃ1. ሁሉንም ድብልቅ ቁጥሮች ወደ ህገወጥ ክፍልፋይ ለውጡ።

ደረጃ2. አካፋይ ገልብጡ (ተገላቢጦሻቸውን ውሰዱ ከዚያም አባዙ መልሳችሁ ህገወጥ ከሆነ በዝቅተኛ ሒሳባዊ ቃል ግለጹ) ምሳሌ $2\frac{3}{4} \div 1\frac{5}{6} = \frac{11}{4} \div \frac{11}{6} = \frac{11}{4} \times \frac{6}{11} = \frac{66}{44} = \frac{3}{2}$

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

4. የሚከተሉትን ክፍልፋዮች አካፍሉ፡፡

ሀ. $\frac{7}{8} \div \frac{5}{6} =$ ---------- ለ. $\frac{2}{3} \div \frac{5}{7} =$----------

5. የሚከተሉትን ድብልቅ ክፍልፋዮችን አካፍሉ

ሀ. $5\frac{1}{4} \div 1\frac{1}{9} =$ ---------- ለ. $2\frac{2}{3} \div \frac{1}{6} =$ ----------

ሁለተኛ ሳምንት

ማስታወሻ፡- አስርዮሾችን መደመር

ደረጃ1. አስርዮሽ ነጥቦችን በመስመር ማስቀመጥ

ደረጃ2. ሁለቱን ቁጥሮች ተመሳሳይ የአስርዮች ቤቶች ብዛት እንዲኖራቸው በጐደሉት ቦታዎች ዜሮዎችን ፃፍባቸው፡፡ ምሳሌ ሀ 24.5+37.12 = 24.50 ለ. 234.62

+37.12 + 865.30

61.62 1099.92

6. የሚከተሉትን አስርዮሽ ደምሩ

ሀ. 85.7 +67.3 = ---------- ለ. 23.15+64.5 = ----------

አስርዮሾችን መቀነስ

ደረጃ1. የአስርዮሽ ነጥቦችን በመስመር ትይዩ ማስቀመጥ

ደረጃ 2 ሁለቱን ቁጥሮች ተመሳሳይ የአስርዮሽ ቤት እንዲራቸው በጉደሉት ቦታዎች ዜሮዎችን ካስፈለገ በስተመጨረሻው መጨመር

ደረጃ3. ሙሉ ቁጥሮችን በምትቀናንሱበት ዘዴ መቀነስ

ምሳሌ ሀ. 1.35 - 0.3 = -------- ለ. 543.431- 41.35----------

1.35 543.431

- 0.30 - 41.350

1.05 502.081

7. የሚከተሉትን አስርዮሽ ቀንሱ ሀ. 4.623-3.25= ---------- ለ. 20.639-12.84= -------

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

ሶስተኛ ሳምንት

ማስታወሻ፡- አስርዮሾችን ማባዛት

ደረጃ 1- የአስርዮሾችን ነጥቡን ከግምት ስናስገባ እንደሙሉ ቁጥሮች ማባዛት

ደረጃ 2- በአብዛኛውና በተበገረው አስርዮሽ ላይ ያሉትን የአስርዮሽ ቤቶች መቁጠርና ብዛታቸውን መለየት

ደረጃ 3- ከብዜቱ ቁጥር ከቀኝ በኩል በመጀመር ወደግራ በደረጃ 2 የደመራችሁትን ብዛት ያህል የአስርዮሽ ቤቶች ቁጠሩ፡፡ የአስርዮሽ ነጥቡን በደረጃ 2 ቆጥራችሁ ካገኛችሁት ጋር ተመሳሳይ በማድረግ አስቀምጡ፡፡ በድምሩ ያገኛችሁንት የአስርዮሽ ቤት ብዛት ከብዜቱ የአስርዮሽ ቤቶች ብዛት ከበለጠ ከብዜቱ ፊት ለፊት ዜሮዎችን አስቀምጡ፡፡

ምሳሌ ሀ. 5.2 x 1.3 = ---- 5.2 x 1.3 = 156 + 52 = 6.76

ለ. 6.13 x 2.5 =---- 6.13 x 2.5 = 3065 + 1226 = 15.325

8. አስርዮሾችን አባዙ ሀ. 5.6 x 7.6 = ---------- ለ- 5.35 x 0.84 = --------

9. > ፣ < ወይም እኩል ይሆናል የሚሉትን ምልክቶች በመጠቀም አወዳድሩ

ሀ. 3.2 x 2.4 ---------- 5.1 x 1.2 ለ 0.86 x 0.8 -------- 0.1 x 8.6

አስርዮሾችን ማካፈል

ደረጃ 1- የአስርዮሽ ነጥቡን ወደቀኝ ቢወሰድ አካፋዩን ሙሉ ቁጥር አድርጉ፡፡

ደረጃ 2- በተከፋዩ ውስጥ ያለውን የአስርዮሽ ነጥብ አካፋይ ላይ ያለውን ነጥብ በወሰዳችሁት ቦታ መጠን ወደ ቀኝ አንቀሳቅሱት ፡፡ በቂ የሆነ ቁጥር ከሌለ በተካፋዩ በቀኝ በኩል ዜሮዎችን ጨምሩ፡፡ ደረጃ 3- በተለመደው ዘዴ አካፍሉ

ምሳሌ ሀ- 8 ÷ 0.5 = $\frac{8}{0.5} \times \frac{10}{10} = \frac{80}{5} = 16$ ለ. 0.36 ÷ 0.04 = $\frac{0.36}{0.04} \times \frac{100}{100} = \frac{36}{4} = 9$

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

10. አካፍሉ ሀ. 12÷0.06 ለ. 19.6 ÷ 0.14

ማስታወሻ፡-አስርዮሾችን አስር ርቢዎች ማካፈል

- አንድን አስርዮሽ በአስር፣ በመቶ፣ በሽ ወዘተ በማካፈል በተካፋዮ ውስጥ ያለውን የአስርዮሽ ነጥብ ወደ ግራ በአካፋዩ ላይ ባሉት ዜሮዎች ልክ ውሰዱት፡፡

ምሳሌ ፡- ሀ. 0.8 ÷10 = 0.08 ለ. 12.6 ÷100 = 0.126

11. አካፍሉ ፡- ሀ. 4.27 ÷10 = ---------- ለ 4.27 ÷1000 = ----------

አራተኛ ሳምንት

ምዕራፍ -4 መረጃ አያያዝ ባር ግራፎችን መሥራትና መተርጐም

ማስታወሻ፡- የመረጃ አያያዝ ማለት መረጃዎች የምናሰባስብበት፣ የምናቀናጅበትና የምናጠቃልልበት ዘዴ ነው፡፡ መረጃዎቹ ተሰባስበው ግራፍ ሠርተን በምናሳይበት ጊዜ የመረጃዎችን ዝርዝር ሁኔታ በጥልቀት ለማጥናት ያስችለናል፡፡ ባርግራፍ በእያንዳንዱ ባር መካከል እኩል ርቀትና ተመሳሳይ ስፋት ባላቸው ባሮች አማካይነት በቁጥር የተገለፀ መረጃን ለመወከል የምንጠቀምበት ስዕላዊ መግለጫ ነው፡፡ ባር ግራፍ አምዳዊ ወይም አግዳሚ ሊሆን ይችላል፡፡

12. **የሚከተለውን ሠንጠረዥ በመጠቀም በሥሩ የተቀመጡትን ጥያቄዎች ሥሩ**

የፍራፍሬ ዓይነት	የመራጭ ተማሪዎች ብዛት
ሙዝ	6
አናናስ	7
ማንጐ	11
ብርቱካን	5
ፖፖያ	8

ሀ. ሠንጠረዡን በመጠቀም ባርግራፍ ሥሩ


ለ. ከሁሉም አነስተኛው ተወዳጅ ፍራፍሬ የቱ ነው ?

ሐ. ከፍራፍሬዎች ሁሉ ይበልጥ ተወዳጅ የሆነው የቱ ነው?

መ. በመረጃ አሰባሰቡ የተካተቱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

13. የሚከተለው ባር ግራፍ የሚያሳየው በአንድ መንደር ውስጥ ያሉ ህፃናት ዕድሜ ነው



ሀ. ዕድሜያቸው ከ11 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ስንት ናቸው?

ለ. ዕድሜያቸው 14 ዓመት የሆኑ ህፃናት ስንት ናቸው?

ሐ. ዕድሜያቸው ከ12 ዓመት በላይ የሆኑ ህፃናት ስንት ናቸው?

መ. በድምሩ ውስጥ በጠቅላላው ስንት ህፃናት ይገኛሉ?

አምስተኛ ሳምንት

ማስታወሻ፡- የቁጥር አማካይ አማካይ የሚባለው የቁጥሮች ጠቅላላ ድምር ለቁጥሮች ብዛት ተካፍሎ የሚገኝ ቁጥር ነው፡፡

14. በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ 10 ተማሪዎች የሒሳብ ሙከራ ውጤታቸው እንደሚከተለው ነው፡፡11፣ 15፣ 8፣ 18፣ 16፣ 12፣ 13፣ 16፣ 9 እና 10 ቢሆን አማካይ ውጤታቸው ስንት ነው?

ቀናት	ሰኞ	ማክሰኞ	ረቡዕ	ሐሙስ	ዓርብ	ቅዳሜ	እሁድ
የጎብኝዎች ብዛት	54	65	80	75	84	95	130


ሀ. የሳምንቱ አማካይ የጎብኝዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. ከአማካይ በላይ የሆነ ብዛት ያለው ጎብኝዎች የመጣበት በየትኛው ቀን ነበር?

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

ምዕራፍ 5 የጅኦሜትሪ ምስሎችና ልኬት


- ቀጥታ መስመር በተቃራኒ አቅጣጫ እየቀጠለ ወይም እየረዘመ የሚሄድ የነጥቦች ጥርቅም ነው። ⟷ ቀጥታ መስመር
- ትይዩ መስመሮች በአንድ ጠለል ላይ ያሉና ምንጊዜም የማይቋረጡ መስመሮች ትይዩ መስመሮች ይባላሉ። ⟷ ⟷ ትይዩ መስመሮች
- ቀጤነክ መስመሮች በመዕዘናዊ አንግል (90^0) ላይ የሚቋረጡ መስመሮች ናቸው



ቀጤ ነክ መስመሮች

- ውስን ቀጥታ መስመር የምንለው የቀጥታ መስመሩ መነሻና መድረሻ ያለው ሆኖ በውስጡ ያሉትን የነጥቦች ስብስብ ነው ——— ውስን ቀጥታ መስመር

15. ምስሉን በመጠቀም የሚከተሉትን ሰይሙ



ሀ. ውስን መስመር

ለ. ነጥቦች

ሐ. ተቋራጭ መስመሮች

መ. ትይዩ መስመሮች

ስድስተኛ ሳምንት

ውስን ቀጥታ መስመርን ለሁለት እኩል መግመስ

አንድን ውሰን መስመር መግመስ ማለት ውስን መስመሩን ወደ ሁለት እኩል ውስን መስመሮች መክፈል ነው። አንድን ውስን ቀጥታ መስመርን ለመግመስ የሚያገለግሉ /የሚያስፈልጉ/ ቁሳቁሶች ማስመሪያ፣ ወረቀት ፣ ኮምፓስ፣ እርሳስ፣ ላጲስ ወዘተ ናቸው

16. በተሰጣችሁ ልኬት መሠረት ውስን ቀጥታ መስመሮችን ሥሩ። ከዚያ እያንዳንዱን ውስን ቀጥታ መስመር ለመግመስ ማስመሪያና ኮምፓስ ተጠቀሙ

ሀ. 6 ሳ.ሜ ለ. 9 ሳ.ሜ ሐ 12 ሳ.ሜ መ 7 ሳ.ሜ


በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

ማስታወሻ፡- ቀጤነክ መስመሮች የሚባሉት በአንድ ጠለል ላይ የሆኑና በማዕዘናዊ አንግል የሚቋረጡ መስመሮች ናቸው፡፡

17. ለእያንዳንዱ ምስል በተሰጠው ነጥብ የሚያልፍና ለተሰጠው መስመር ቀጤ የሆነ መስመር ሥሩ፡፡ ሀ. . በ ወ ለ. . ዘ ጠ

ማስታወሻ፡-

ሁለት ውሰን መስመሮች ወየም ጨረሮች የጋራ መነሻ ሲኖራቸው አንግል ይሰራሉ፡፡ ውሰን መስመሮቹ ወይም ጨረሮቹ የሚገናኙበት ነጥብ የአንግሉ መለያያ ይባላል፡፡አንግል በመለያያው ሊሰየም ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንግል “ለ” ለማለት ወይም <“ለ” እንደሁም <ሀለመ ወይም <መለሀ ብሎ መሰየም ይቻላል



18. አንግሎችን ሰይሙ ሀ. ወ ሀ ለ ለ. ጠ በ ዘ

ሰባተኛ ሳምንት

ማስታወሻ፡-

የአንግል መጠን መለኪያ መሳሪያ ፕሮትራክተር ይባላል፡፡አንግሎች በልኬታቸው መጠን ሲመደቡ ሹል፣ ማዕዘናዊ፣ ዝርጥ፣ ዝርግ እና ጥምዝ አንግል በመባል ይመደባሉ፡፡

1. ሹል አንግለ የሚበለው ልኬቱ በ0^0 እ 90^0 መካከል የሆነ አንግል ነው፡፡
2. ማዕዘናዊ አንግል የሚባለው ልኬቱ 90^0 የሆነ አንግል ነው፡፡
3. ዝርጥ አንግል የሚባለው ልኬቱ ከ90^0 የሚበልጥ ነገር ግን ከ180^0 የሚያንስ አንግል ነው፡፡
4. ዝርግ አንግል የሚባለው ልኬቱ 180^0 የሆነ አንግል ነው
5. ጥምዝ አንግል የሚባለው ለኬቱ ከ180^0 የሚበልጥና ከ360^0 የሚያንስ አንግል ነው፡፡

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

19. በ"ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት አንግሎች ከ"ለ" ረድፉ ልኬታቸው ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. ዝርጥ አንግል	ሀ. 270^0
2. ሹል አንግል	ለ. 144^0
3. ማዕዘናዊ አንግል	ሐ. 29^0
4. ዝርግ አንግል	መ. 90^0
5. ጥምዝ አንግል	ሠ. 180^0

ማስታወሻ፡- አንግልን መግመስ የ< "ሀ" ልኬት ከ "ረ" ልኬት ጋር እኩል ከሆነ<ሀ ከ "ረ" ጋር ተጋጣሚነው ይባላል። ይህ በምልክት ሲገለጽ <ሀ ≡<ለ። አንግልን ለመግመስ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማስመሪያ፣ ኘሮትራክተር ፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ላጲስ

20. በምስሉ ላይ የተሰጣቸሁን አንግል በአንግል መግመስ ቅደም ተከተል ተጠቅማችሁ አንግሉን ከሁለት አኩል ግመሱ። ሀ. ሠ መ ረ ለ. ቀ ሸ በ

ስምንተኛ ሳምንት

ጎነ ሶስቶች በጐኖቻቸው መሠረት በሦስት መመደብ ይቻላል።


1. ሶስቱም ጎኖቹ እኩል ያልሆኑ ጎነ ሶስት ጎኖቹ **የተለያዩ ጎነ ሶስት** ተብለው ይጠራል።
2. ሁለት እኩል ጐን ያለው ጎነ ሶስት **ሁለት እኩል ጐን ጎነ ሶስት** ተብሎ ይጠራል።
3. ሦስቱም ጎኖቹ እኩል የሆነ ጎነ ሶስት **እኩል ጎን ጐነ ሶስት** ተብሎ ይጠራል።

ጎነ ሶሰቶች በአንግሎቻቸው አማካይነት በሦስት ይመደባሉ።

1. **ሦሰቱም** አንግሎቹ ሹል አንግል ከሆነ **ሹል አንግል** ጐነ ሶስት ይባላል።
2. የአንዱ አንግል ልኬት ዝርጥ ከሆነ ጐነ ሶስቱ **ዝርጥ አንገል** ጎነ ሶስት ይባላል።
3. የአንድ አንግል ልኬት 90^0 ከሆነ ጐነ ሶስቱ **ማዕዘናዊ አንግል** ጎነ ሶስት ይባላል።
4. የአንድ ጐነ ሶስት ሦስቱም አንግሎች መጠን እኩል ከሆነ **ጐነ ሶስት እኩል አንግል ጎነ ሶስት** ይባላል።አስተውሉ፡- የማንኛውም ጐነ ሶስት የሦስት አንግሎች ልኬት ድምር 180^0

በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች

21. የሚከተሉትን ጎን ሶስቶች በአንግሎቻቸውና በጐኖቻቸው መጠን ሰይሙ፡፡



22. ማስመሪያና ኘሮስራክተር በመጠቀም የሚከተሉትን ጐነ ሶስቶች ንድፉ

ሀ. ሁለት እኩል ጐን ጐነ ሶስት

ለ. እኩል ጐን ጎነ ሶስት

ሐ. ዝርጥ አንግል ጎነ ሶስት

መ. ማዕዘናዊ አንግል ጎነ ሶሰት

ሠ. ማዕዘናዊ አንግልና ሁለት እኩል ጐን ጎነ ሶስት

ዘጠነኛ ሳምንት


- የሬክታንግል ዙሪያ ሁለት ጊዜ ርዝመት (ር) ሲደመር ሁለት ጊዜ ወርድ (ወ) ነው፡፡
  ዙሪያ (ዙ) = 2ር+2ወ = 2(ር+ወ)
- የካሬ ዙሪያ = ር +ር+ ር+ ር = 4xር እያንዳንዱ ጐን ርዝመት ዙ= 4xርዝመት ወይም ዙ= 4ር
- የሬክታንግል ስፋት የርዝመትና የወርድ ብዜት ነው፡፡
  ስ= ርወ ፣ ስ - ስፋት ር - ርዝመት ወ - ወርድ
- የሬክታንግል (ስ) = የአንድን ጐን ርዝመት ካሬ ነው፡፡የኮሬ ስፋት (ስ) = ር x ር= $ር^2$

23. የሚከተሉትን ምስሎች ዙሪያና ስፍት ፈልግ/ጊ/

ሀ



ለ.



በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ማስተማር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ለተማሪዎች የተዘጋጁ የ5ኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርት ጥያቄዎች


24. 16 ሜ በ10 ሜ የሆነውን የቤት ወለል ለመሸፈን እያንዳንዳቸው 1 ሜ በ1 ሜትር የሆኑ ስንት የወለል ጡቦች ያስፈልጋሉ?

አስር ሳምንት

ማስታወሻ፡-

- ኘሪዝም ወርድ ፣ ርዝመትና ቁመት ያለው ጠጣር ምስል ነው፡፡ ኩብ ርዝመቱ ፣ ወርዱና ቁመቱ እኩል የሆነ ኘሪዝም ነው፡፡
- ኘሪዝም ስፍት (ስ) =2 (ርዝመት x ወርድ + ርዝመት x ቁመት) = 2 (ርወ +ርቁ + ወቁ)
- የኩብ ገፆች ስፋትን ለማግኘት እያንዳንድ ኩብ ገጽ እኩል ስፋት ያለው በመሆኑ ስፋት (ስ) = 6 x (ርዝመትxርዝመት) = 6 x $ር^2$
- የጠጣር ምስል የሚይዘው ቦታ መጠን ይዘት ይባላል፡፡የሬክታነግላዊ ኘሪዝም ይዘት (ይ) = ርዝመት x ወርድ x ቁመት ይ = ር x ወ x ቁ፡፡
- የኩብ ይዘት (ይ) = ርዝመት x ርዝመት xርዝመት (ርዝመት= ወርድ = ቁመት ይ = $ር^3$


25. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ



ሀ. ስፋቱን አስላ/ይ/

ለ. ይዘቱን አስላ/ይ/

26. ለሚከተለው ኩብ ስፋቱንና ይዘቱን አስሉ፡፡



27. በጐን ርዝመቱ 4 ኩቦች፣ በወርድ 6 ኩቦች እንዲሁም ለቁመቱ 5 ኩቦች የያዘ ሳጥን ይዘቱ ስንት ነው?

28. የአንድ ሬክታንግላዊ ኘሪዝም ቁመቱ 6 ሳ.ሜ፣ ወርድ 4 ሳ.ሜ እና ርዝመት 8 ሳ.ሜ ቢሆን ስፋቱ ስንት ይሆናል?